# ርእሰ አንቀጽ

«ዘበእንቲሃ ለቤተ ክርስቲያን ተደፋእከ በውስተ ዓውድ»
ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ክርስቲያኑ ሕዝብ ድኅነት በአደባባይ ተዋረድክ፣ ተገፈፍክ፣ ተገረፍክ።

መድኃኔ ዓለም የሚለው ስሙ ከዚህ ጥቅስ ጋር ይስማማል። የዓለሙ ሁሉ መድኃኒት ለመሆን ስለ ዓለም ስትል ተደፋህ፣ ተገረፍክ፣ ተመታህ ግን ለዓለም ሁሉ ቤዛ መድኃኒትም ሆንክ።

ክርስቶስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ራሱን እንደሰጠ፣ መስዋዕትም እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ... ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደ ስለ እርስዋም ራሱን እንደለወጠ ያስረዳናል። (ኤፌ. 5፥25) ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ የሞተላት ተቋም ናት ግን እርሷን ቤ ተ ክርስቲያንን የሕይወት መዝገብ አድርጓታል፣ ከእርሷ ውጭ ድኅነት እንደሌለ አድርጎ አቋቁሟታል።

ክርስቶስ ሐዋርያትን ጥብቅ መሠረት አድርጎ በሐዋርያት መሠረት ላይ ቤተ ክርስቲያንን አንጿታል። «እኔም እልሃለሁ አንተ ድንጋይ ነህ በዚችም ድንጋይ ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ። የገሃነም ደጆች አይገለብጧትም።» ሲል ራሱ ክርስቶስ የተናገ ረው ቃል ያስረዳል። (ማቴ. 16፥18) ይህን ተከትሎ ቅዱስ ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መሠረት ጥብቅ እንደሆነ ክርስቶስ «በሐዋርያትና በነቢያት መሠረትነት እንደመሠረቷት በ ሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ተሰራችሁ፣ የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ እርሱ ኢየሱስ ክርስ ቶስ ነው።» ሲል ቤተ ክርስቲያንን ጊዜያዊ፣ ቅጽበታዊ፣ የይድረስ ሥራ አለመሆኗን ገልጦ ተናግሮታል። (ኤፌ. 2፥20)

ይህችን ቤተ ክርስቲያን የእርሱ ምድራዊ መንግሥቱ አድርጎ ሕጉ የሚነገርበት፣ ስሙ የሚቀደስበት አድርጓታል። ይህችን ቤተ ክርስቲያን አሁንም የሚጠብቅ ስለ እርሷ የሚናገር፣ የሚሰራ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ነው። ስለዚህ እኛ ቤተ ክርስቲያንን በተቀበልን በት መልክ መጠበቅ አለብን፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ክብር፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ሲ ል ክርስቶስ ሕማምን መከራ መስቀልን ተቀብሏልና። ስለ ቤተ ክርስቲያን አሁንም የሚሰራ ፣ የሚናገር መድኃኔዓለም ክርስቶስ ስለሆነ የቤተ ክርስቲያንን ቅድስናዋን ሐዋርያዊ ጠባይ ዋን መጠበቅ አለብን።

ክርስቶስ ራስ የሚሆነን እኛም አካሉ የምንሆን ቤተ ክርስቲያን ሆነን ተሰርተን፣ ቤተ ክርስቲያን ሆነን ለእርሱ ማደሪያነት በቂ ሆነን ስንገኝ ነው። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ «እርሱም የሥጋው የቤተ ክርስቲያን ራስ፣ እርሱም መጀመሪያ የሙታን በኲር እርሱ በፊት ይሆን ዘንድ በሁሉ» ሲል የክርስቶስን ራስነት፣ የእኛን አካልነት በቤተ ክርስቲያን አማካይነት የሚገኘውን ግንኙነት ገልጦ ያስተምራል። (ቈላስ. 1፥18)

ቤተ ክርስቲያን የምሥጢራት መዝገብ፣ የምሥጢራት ፈጻሚ ሆና በመገኘቷ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካልነቷን፣ ክርስቶስ ከእርሷ የማይለያት መሆኑን እንረዳለን።

እንግዲህ ክርስቶስ በደሙ የመሠረታትን ቤተ ክርስቲያንን ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲል ክርስቶስ መከራ መስቀልን የተቀበለላትን እኛ እንደ ዓይነ ብሌን አድርገን መጠበቅ፣ እንደ ዓላማዋም መፈጸም ግድ ይኖርብናል።

ቤተ ክርስቲያንን እንደ ዓላማዋ በመፈጸም ካልጠበቅናት፣ ዓላማዋን ከረሳን ክርስቶስ ስለ እርሷ መሞቱን መከራ መስቀሉን መርሳታችን ነው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያንን ዓላማ ጠንቅቀን ማወቅ እንደዓላማዋም ፈጻሚዎች ሆነን መገኘት የሁላችን ግዴታችን ይሆናል።

በቤተ ክርስቲያን አንጻር ደግሞ የእኛ አካል፣ የእኛ ልቦና የእግዚአብሔር ቤተ

መቅደስ እንደሆነ እርሱም የእግዚአብሔር ማደሪያ እንደሆነ እርሱም በንጽሕና በቅድስና መያዝ አስፈላጊ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይነግረናል «አላወቃችሁምን እናንተ የእግዚአብሔር መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ አድሮባችኋል። ማንም የእግዚአብሔርን መቅደስ ቢያጠፋ እርሱንም እግዚአብሔር ያጠፋዋል። የእግዚአብሔር ቤት የተቀደሰ ነውና፣ ያውም እናንተ ናችሁ።» (1ኛ ቆሮ. 3፥16) ራሳችን ቤተ ክርስቲያን መሆናችን ራሳችንን መጠበቃችን ተገቢ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ ሰፋ አድርጎ የገለጠው ራሱን ከቶ የሚጠላ የለም ይመግበዋል፣ ይንከባከበዋል እንጂ፣ እንግዲያውስ የክርስቶስ ማደሪያ ለመሆን የተሰራን ቤተ ክርስቲያን መሆናችን እንወቅ፣ እንደ ቤተ ክርስቲያንነታችን የክርስቶስ ማደሪያዎች ለመሆን እንዘጋጅ። ክርስቶስ ስለ ቤተክርስቲያን መከራን ተቀብሏልና፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲል ራሱን መስዋዕት አድርጓልና።

**ከብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ**

---

# <u>የአስተዳደሩ ቦርድ ሪፓርት</u>

## <u>የካቴድራላችን ዕድገት</u>

የዛሬ አሥራ አምስት ዓመት በበርክሌይ ከተማ መካነ ሰላም መድኃኔ-ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ በጥቂት ምዕመናንና የኃይማኖት አባቶች የተቋቋመው ዛሬ ደረጃ በደረጃ በስምም ሆነ በግብር እያደገ መጥቶ ስሙ ከቤተ ክርስቲያንነት ወደ ካቴድራልነት ተሸጋግሯል።

በዚያን ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ወደ ኋላ መለስ ብለን በዓይነ ሕሊና ብንቃኝ እዚህ ደረጃ ላይ የተደረሰው «አልጋ በአልጋ» በተደረገ ለስላሳ ጉዞ ሳይሆን ውጣ ውረዱን፤ ጠመዝማዛና ፈታኝ ወቅቶችን በጠንካራ የሃይማኖት አባትና በጥቂት የአመራር አባላት በተደረገ ከፍተኛ ጥረት ነው። ዕድገቱም በስም ብቻ ሳይሆን በተግባርም በብዙ ቦታዎች ላይ ታይቷል። ይኸውም፥

1ኛ) ካቴድራሉ በአሁኑ ወቅት የሚተማመንባቸው ከአራት መቶ በላይ የሚሆኑ አባላትን አፍርቷል። ለዚህ ነው የካቴድራሉ ዕድገት በየደረጃውና በየወቅቱ ሊመዘገብ የቻለው። ባሳለፍነው በ1998 ዓ.ም. እንኳ ከካቴድራሉ ጋር ኩታ ገጠም የሆነ አንድ የመኖሪያ ቤት ገዝቶ የካቴድራሉን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ወደ $፮ ሚሊዮን (ስድስት ሚሊዮን ዶላር) ከፍ አድርጎታል። አሁንም ቢሆን ዕድገቱ በዚህ ላይ ይደመደማል ማለት አይደለም። ይልቁንስ የእኛ ተስፋና እምነት፤ ደስታችንም ካቴድራሉ የራሱን የገቢ ምንጭ መሥርቶ፤ የገንዘብ ፍላጎቱን አሟልቶ አንድ ካቴድራል ሳይሆን ሁለት ሦስት ከዚያም በላይ በማስመዝገብና ደከምያሉ አብያተ ቤተ ክርስቲያናትን የመደጐም አቅም ሲኖረው ነው ብለን እናምናለን።

2ኛ) ዕድገቱ በሚንቀሳቀስና በማይንቀሳቀስ ንብረት ብቻ አይለካም። ለረጅም ጊዜያት በአንድ ዲያቆን ብቻ ሥርዓተ ቅዳሴ ይካሄድ የነበረው እነሆ ዛሬ እዚሁ በቤታችን (በካቴድራላችን) ውስጥ ያፈራናቸው ሁለት ዲያቆናት በብፁዕ አባታችን በአቡነ መልከጸዴቅ የድቁና ክሕነት ተሰጥቷቸው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። በዚህ ዓይነት ነገ ደግሞ ቀሳውስትን የማናፈራበት ምንም ምክንያት የለም ብለን እናምናለን። ራስን በራስ ከመቻል የበለጠ ምን የሚያረካ ነገር ይገኛል?

3ኛ) ባሳለፍነው የሱባኤ ወቅትም ዕለት በዕለት ምህላ ሲደረግ የወንጌል ትምህርት ሲሰጥ ቆይቷል። ዓርብ ዓርብ የሚስጠው የወንጌል ትምህርት አሁንም እንደቀጠለ ነው። በዚህ አቅጣጫ የምዕመናኑ ተሳትፎ አመርቂ በመሆኑ ጉባኤው እያደገ መቷል።

ተጨማሪ የሃይማኖት አባት ቀሞስ አባ ፍሬ ሃይማኖትን በማግኘታችንም የወንጌል ትም ህርቱ እየተጠናከረ እንደሚሄድ ይታመናል። በተደጋጋሚ የተደረጉ የሃይማኖት ጉባኤዎ ችም የምዕመናኑን መንፈስ የሳቡና ሰለ ሃይማኖታቸውም ሰፊ ግንዛቤ እንዳገኙ የጉባኤ ው ተሳታፊዎች ይናገራሉ።

4ኛ) በአሁኑ ጊዜ ምዕመናኑ ተሰጥኦ የመቀበል ባህርይ እያዳበሩ መጥተዋል። ይ ህም ሊሆን የቻለው በኮምፒዩተር አማካኝነት ቅዳሴውንና መዝሙሩን በሰሌዳ ላይ ፊት ለፊት ለማንበብ በመቻላቸው ነው። ይህን ሰሌዳ ገዝተው ያበረከቱልንን ምዕመናን እያ መሰገንን ለእኛ እንዳሰቡልን ለእነሱም መድኃኔ ዓለም አሳቢ ይሁንላቸው እንላለን። ፕሮግራሙንም ደግሞ ዘወትር ተግባራዊ ለሚያደርጉልን፤ መዝሙሩንም በመሪነት የሚያ ካሂዱትን የሐመረ ኖሕ መዘምራንንም እያመሰገንን ይህ ትብብራቸው በሰፊው እንደሚ ቀጥልም እንተማመናለን።

5ኛ) በታዳጊ ወጣቶች በኩል ስንመለከትም የትምህርት ኰሚቴ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ አደረጃጀቱና አመራሩ በአሁኑ ጊዜ ለየት ያለ ነው። የሃይማኖት፣ የመዝሙ ርና የአማርኛ ፊደል ትምህርት ከመስጠቱም በላይ ሕጻናት ከቁርባን በኋላ ከቦታ ቦታ በመሯሯጥ ለአደጋ እንዳይጋለጡ በተለያየ ሥራዎችም ተጠምደዋል። ጐበዝና ባለሙያ የሆኑ መምህራን በመሳተፋቸው ታዳጊ ወጣቶች ባስተሳሰብ እየጐለበቱ እንደመጡ ይታ መናል። መምህራኑም ያለማቋረጥ በየሳምንቱ እየተሰበሰቡ ሰለትምህርቱ ይዘትና ሂደት በሃይማኖት አባቶች በተከታታይ ስልጠናና መመሪያ ሰለሚሰጣቸው ውጤቱ አሰደሳች ሆ ኗል። ከህፃንነት ጀምሮ እዚሁ ሰንበት ት/ቤት ፊደል ቆጥረው ያደጉ ወጣቶች ጥቂቶቹ ዛሬ በኰሌጅ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ነው። ለሚቀጥለው የትምህርት ዘመን ደግ ሞ ቁጥራቸው በርከት ያሉ ወጣቶች ወደ ኰሌጅ ይሄዳሉ። የትምህርት ኰሚቴው ቀደ ም ብለው ወደ ኰሌጅ የሄዱትን ወጣቶች በሰንበት ትምህርት ቤት ተገኝተው የመጀመ ሪያ ዓመት የኰሌጅ ልምዳቸውንና የሽግግሩን ወቅት እንዴት እንዳዩት ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ተጋብዘዋል። እንዲህ ዓይነቱ አመለካከትና አስተሳሰብ ሁላችንንም ሊያሰ ደስት የሚገባውና ቀጣይነትም ይኖረዋል ብለን እናምናለን። ትናንት በእጠገባችን ድክ ድክ ሲሉ የነበሩት ሕፃናት ዛሬ እዚህ ደረጃ ደርሰው ስንመለከት መድኃኔ ዓለም ይመስ ገን ከማለት በሰተቀር ሌላ ምን እንላለን !!!

6ኛ) ከዚህ በፊት ደጋግመን እንደገለጽነው ሁሉ ያለን የመተዳደሪያ ደንብ አሁን ከደረስንበት የዕድገት ደረጃ ጋራ ሲመዘን በቂ ሰላልነበረ ይህ መተዳደሪያ ደንብ ተሻሽ ሎ በህዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ለሰበካ ጉባኤ አባላት ቀርቧል። በዚህም ዕለት የካቴድ ራሉ የሒሳብ ሪፖርትም በኦዲተሮች ተነቧል። የሰበካው ጉባኤም የሒሳብ ሪፖርቱን ሙሉ በሙሉ ሲያፀድቅ የመተዳደሪያ ደንቡን ግን አንዳንድ ማሻሻያ ካደረገ በኋላ በከ ፍተኛ ድምፅ ተቀብሎ አጽድቆታል። በዚህም ዕለት የሰበካው ጉባኤ በተሰጠው ሥልጣ ን መሠረት አምስት የአስመራጭ ኰሚቴ አባላትን መርጦ ለሦስት ዓመታት የሚመሩት ን የአመራርና የኦዲት አባላት ለማስመረጥ ሥራውን እያጣደፈ መሆኑን ተገንዝበናል። እያንዳንዱ አባል እኔ ለሃይማኖቴ ዘብ እቆማለሁ፤ ዘወትር ተገልጋይ ከመሆን አገልጋይ መሆንን እመርጣለሁ ብሎ መወዳደር መብቱም ግዴታውም መሆኑን ማስገንዘብ እንወዳ ለን።

## ማጠቃለያ

ለዚህ ካቴድራል ዕድገት ጉልበታቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ እውቀታቸውንና ጊዜያቸ ውን የሚሰው አያሌ ናቸው። እያንዳንዱን አባል በዚህ ሪፖርት መጥቀስ አስቸጋሪ ሰለ ሆነ እንዲያው በጥቅሉ ምስጋና እናቀርባለን። በተለይ ደግሞ ከበርክሌይ ከተማ ከመጣ

ን ጊዜ ጀምሮ ፀሐዩ፤ ብርዱ፤ ዝናቡ ሳያግዳቸው የግቢውን አትክልት በመከርከምና ቆሻሻውን በመሰብሰብና በመጣል፣ መኪናዎች ከሥነ-ሥርዓት ውጪ እንዳይቆሙና መተላለፊያ እንዳይዘጉ፤ ወደ ግቢ መግቢያ በሮች ክፍት ሆነው ለውጭ ሰዎች መተላለፊያና መቆሚያ እንዳይሆኑ በራሳቸው ፍላጐት ተነሳስተው አስተዋጽዖ ላደረጉልንና አሁንም ለሚያደርጉልን የአስተዳደር ቦርዱ ከልብ የመነጨ ምሥጋና ያቀርባል

---

## <u>የሐመረ ኖህ ሰንበት ትምህርት ቤት ዓመታዊ እንቅስቃሴ</u>

ይህ ሰንበት ት/ቤት ከተቋቋመ ፲ ፬ አመታትን ቢያስቆጥርም ከአመት ወደ አመት የአባላቱ መንፈሳዊ እድገት እጅግ እየተሻሻለና እየሰፋ መጥቷል። የሰንበት ት/ቤት ዋንኛ አገልግሎት መንፈሳዊ የመዝሙር አገልግሎትን መስጠት ቢሆንም፥ ማህበሩ በገንዘብ ማሰባሰብ፣ መንፈሳዊ ጐባኤዎችን፣ አጫጭር ድራማዎችን በማዘጋጀት፣ የቤተ ክርስቲያኑን አባላት በማሳተፍ የተለያዩ እርዳታዎችን ግንባር ቀደም ሆኖ ለቤተ ክርሰቲያኗ እንዳስፈላጊነቱ ያበረክታል።

<u>በዓመት ውስጥ የተከናወኑ በጐ ተግባሮች</u>

– ለቤተ ክርስቲያኑ ገንዘብን ለማሰባሰብ በየአመቱ የሚያደርገውን የመኪና አጠባ ለሁለት ቀናት በማካሄድ $ ፴ ሺ ዶላር አሰባስቦ ለቤተ ክርሰቲያኑ ገቢ አድርጓል።

– ለቡሄ አመታዊ በዓል መንፈሳዊ ጭውውቶችና ስነጽሁፎችን በአርቲስት ተሰፋዬ ሲማ አዘጋጅነትና አሰልጣኝነት ምዕመናኑን እያዝናና ትልቅ ትምህርትን የሚሰጥ፤ በአይነቱ ለየት ያለ ዝግጅትን አቅርቦ፤ ከአምስት ሺ ብር በላይ ለቤተ ክርስቲያኑ ገቢን አስገብቷል።

– ከቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ በተገዛው ተጨማሪ ቤት ሙሉ የማደስና የማጽዳት ሀላፊነትን ከቦርዱ ተረክቦ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በሚያሰደንቅ ሁኔታ ተግባራዊ አድርጓል።

– መህበሩ ከዚህ በተጨማሪ ለሠርግና ለሀዘን ከቤተ ክርስቲያኑ ሳይለይ የሚያስፈልገውን የመዝሙር አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያኑ አባላት ያበረክታል

– በሚከበረው ዓመታዊ በአል ከየቦታው የሚመጡትን የስንበት ትምህርት ቤት መዘምራን ተቀብሎ ያስተናግዳል

<u>የመህበሩ ውስጣዊ እንቅስቃሴዎች በከፊል</u>

1) ማህበሩ በወር አንድ ቀን ከብፁዕ አቡነ መልከጸዴቅ ጋር በመሰብሰብ የተለያዩ ውይይቶችን፤ መንፈሳዊ ትምህርቶችንና አባታዊ ምክርን ይቀበላል።

2) ይህ ማህበር በመምህር አባ ቃለጽድቅ በተዘጋጀ ያገልግሎትና የወንጌል ትምህርት አባላቱን አስተምሮ ለማስመረቅ የለውን አመታዊ እቅድ ተግባራዊ በማድረግ ሳምንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮርስን በመከታተል ላይ ይገኛል።

የሐመረ ኖህ የሰንበት ት/ቤት ባለው የእርስ በርስ ፍቅርና መግባባት እንዲሁም ባለው የአገልግሎት ጽኑ ፍላጐት ለመጪው ዓመት የተለያዩ የመንፈሳዊ ጉባኤዎችንና የገንዘብ ማስባሰቢያ እንቅስቃሴዎች ለማድረግ አቅዷል ስለዚህም በጉልበት በገንዘብ በሀሳብ ለመርዳት እንዲሁም የማህበሩ አባል በመሆን እንዲሳተፍ ፍቅራዊ ጥሪውን ያቀርባል

የሐመረ ኖህ ስንበት ት/ቤት የመላውን የመድሀኒዓለም ቤተ ክርስቲያን አባላትና ምዕመናን ለሚያደርጉት አባታዊና እናታዊ ምክር፣ በእንቅስቃሴዎቻችን ሁሉ ለምታደርጉት ያላሰለሰ ድጋፍ ታላቅ ምስጋናን ያቀርባል።

«እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንኩት እርስዋንም እሻለሁ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን አይ ዘንድ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ» መዝ. ፳፮፥፬

**የሐመረ ኖህ ሰንበት ት/ቤት**

---



# ዜና ቤተ ክርስቲያን

## የኤጲስ ቆጶሳት ሢመት በዋሺንግተን ዲሲ

ጥር ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በሕጋዊውና አንድያ የቤተ ክርስቲያናችን መሪ በሆኑ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፤ በውጭ አገርና ወደፊትም በምድረ ኢትዮጵያ ሊያገለግሉ የሚችሉ ዘጠኝ አባቶች መነኮሳትን በማዕረገ ኤጲስ ቆጶስነት በዋሺንግተን ዲሲ፤ አራት ኤጲስ ቆጶስነት በካናዳ ቶሮንቶ በድምሩ 13 ተሹመዋል።

ይህ በዓለ ሢመት የተካሄደው በዋሸንግተን ዲሲ በሚገኘው በሕጋዊነት መንፈሳዊ አገልግሎቱን እያካሄደ ባለው በደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራልና በሳምንቱ ደግሞ በቶሮንቶ መንበረ ብርሃን ካቴድራል ነበር። በዚህ ሢመተ ኤጲስ ቆጶስ በዓል ላይ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ሰብሳቢና የቅዱስ ፓትሪያርኩ ረዳት ሊቀጳጳስ፣ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ የአውሮፓና አፍሪካ ሃገረ ስብከት ሊቀጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል፣ ብፁዕ አቡነ መልከ-ጼዴቅ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና የቅዱስ ሲኖዶስ አባልና ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ተቀማጭነታቸውና አገልግሎታቸው በታላቋ ብሪታኒያና አካባቢዋ ሊቀጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል በዚህ ሢመተ ኤጲስ ቆጶስ በዓል ሲሳተፉ ከተለያዩ የአሜሪካ ክፍለ ግዛቶች፣ ከካናዳና አውሮፓ የመጡ ክቡራን ሊቃነ ካህናት፣ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን፣ መዘምራንና ምዕመናን እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው የውጭ አገር የክብር እንግዶች ተገኝተዋል።

በደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ዋሺንግተን ዲሲ ቅዳሜ ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ከ፲ ሰዓት እስከ ፲፪ ሰዓት ጸሎተ አስኬማና የሠርክ ጸሎት ተደረገ። ከሌሊቱ ፲ ሰዓት ለእሁድ አጥቢያ ስብሐተ ማሕሌቱ ተጀምሮ ሲካሄድ አድሮአል።

እሁድ ጥር ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ከጥዋቱ በሁለት ሰዓት ተኩል ጸሎ

ተ ኪዳን ተደርሶ ጸሎተ ቅዳሴው ቀጥ ሏል፣ እርሱም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነጳጳሳ ት ዘኢትዮጵያ መሪነት ከጥዋቱ በሁለት ሰዓት ተኩል ተጀምሮ ወንጌል ከመነበቡ በፊት ሥርዓተ ሢመተ ኤጲስ ቆጶሳት ቀጥሏል። ልዩ ጸሎት ተደርጎለት በእያ ንዳንዳቸው አዲስ ኤጲስ ቆጶሳት በቅዱ ስፓትሪያርኩ እጅ አንብሮተ ዕድ ተፈጽ ሞ፣ ልብሰ ጵጵስና ከተሰጣቸው በኋላ ሁሉም ብፁዓን ሊቃነጳጳሳት «ይደልዋ» ወይም ለእያንዳንዳቸው «ይገባዋል» እ የተባለላቸው ሕዝቡም በአንድ ድምፅ ለእያንዳንዳቸው «ይገባዋል» እያለላቸ ው የመጨረሻው ጸሎተ ሢመት ከተፈጸ መላቸው በኋላ ተሿሚዎቹ ብፁዓን ኤ ጲስ ቆጶሳት በአንድ ድምፅ ቃለ ተዐም ኖ ሰጥተዋል።

ከዚያም ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪ ያርኩና ከብፁአን ሊቃነጳጳሳት ጋር «አሥሉስ ቅዱስ» ከተባለ በኋላ ወደ ፍሬቅዳሴው ገብተው ሥርዓተ ቅዳሴው እንደተጠናቀቀ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መ ርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ዐውደ ምሕረት በተዘጋጀላ ቸው ፓትርያርካዊ መንበር በብፁአን ሊ ቃነጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት፣ ሊቃነ ካህ ናትና ካህናት በቀኝና በግራ ሲቀመጡ ብ ፁዕ አብነ መልከጼዲቅ ሊቀጳጳስና የቅ ዱስ ሲኖዶስ አባልና ዋና ጸሐፊ ስለተፈ ጸመው መንፈሳዊ አገልግሎት መግለጫ ናማሰረጃ ንግግር ያደረጉ ሲሆን ከተለያ ዩየሰሜን አሜሪካ ክፍለ ግዛቶችና እንዲ ሁም ከካናዳና ከአውሮፓ የተውጣጡ መዘምራን ከደ/ኃ/ቅ. ገብርኤል ካቴድራ ል ወጣት መዘምራን ጋር ለተመረጠች ዕለት ያደረሰንን እግዚአብሔርን በዝማ ሬያቸው ከፍ ከፍ አድርገው አመስግነዋ ል።

በተመረጡ የቤተክርስቲያን ሊቃ ውንት ቅኔ የተበረከተ ሲሆን፤ አበርካቾ ችም ሊቀመዕምራን አበባው ይግዛው፣ መምህር ፀጋዬ ስንታየሁ፣ ቀሲስ ዘመነ አቡሃይና መምህር ልዑለቃል አካሉ ናቸው።

ከዚያም የበዓሉ አስተናጋጅ የሆ ነውና የተመረጠው ዕድለኛው የደ/ኃ/ቅ ዱስ ገብርኤል ካቴድራል ሰበካ ጉባኤ ሊቀመንበር አቶ መሃሪ በላይ በእንግሊ ዝኛ በባልቲሞር የመካነ ሰላም ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ሊቀመንበር ዶ/ር አምባቸው ወረታ በአማርኛ በየተ ራ ንግግር ያደረጉ ሲሆን ጥሪ ከተደረገላ ቸው እንግዶችም መካከል በባልቲሞር የአንግሊካን ቸርች ጳጳስ ዘራይት ሪቨረ ንድ ዳንኤል ኮክስና ዶ/ር ሜልበርን ኤ ንትሪም ዲን ኦፍ ዘዋርድ ዩኒቨርሲቲ ስ ኩል ኦፍ ዲቪኒቲ ንግግር አድርገዋል። ከዚያም ብፁአን ኤጲስ ቆጶሳቱ ከካህና ት ጋር ያሬዳዊ ዝማሬ አሰምተው፣ ስለ በዓለ ጥምቀቱና በዓለ አጋዕዝተ ቅድስት ሥላሴ ታቦተ-ሕጉ ወጥቶ ዑደት ተደርጎ ብፅዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትር ያርክ ርዕሰ ሊቃነጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ቃ ለ-ምዕዳንና ቡራኬ ሰጥተው ሠርሆተ ሕ ዝብ ሆኗል። ከዚህም በኋላ ለበዓሉ በ ተዘጋጀው የምሳ ግብዣ ከአዳዲሶቹ ኤ ጲስ ቆጶሳትና ጥሪ ከተደረገላቸው እንግ ዶች ከተለያዩ አገሮች ከመጡ የሰበካ ጉባኤ ተወካዮችና ምዕመናን ጋር ተገኝተዋል።

እግዚአብሔር የከበረበት፣ ቅዱስ ምስጢሩንና ድንቅ ሥራውን ገልጦ ያሳየ በት ዕለት፤ በዚህችም ጥንታዊት ሐዋር ያዊት እናት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ ዋኅዶ ቤተ ክርስቲያን የታየው ድንቅ ሥራ የአምላክ ቅዱስ ፈቃዱ በሆነበት ጊዜ ነው።

የሢመቱ ተግባር በዚህ መልክ ይ ከናወን እንጂ ጸላኤ ሠናያት ለመቃወም መነሣቱ አልቀረም ነበር ይህም ነገር አ ሁንም አምላክን ፊቱን ደፍቶ አሳፍሮት ይገኛል፣ ይኸውም የቀድሞው አባ ጳው ሎስ፣ የአሁኑ አባ ገብረ መድኅን ከተኙ በት ተነስተው የኛን ሥራ ለማጥላላት

ሞክረው ነበር። ቅዱስ ሲኖዶሳችን ግን ጊዜ ሳይወስድ ወዲያው አባ ጳውሎስ የ ነበሩትን አውግዞ ማዕረጋቸውን ገፎ አባ ገብረ መድኅን ብሎ ከቤተክርስቲያን ው ጭ እንዲሆኑ ፤ የመባረክ ፤ የመቀደስ ሥልጣናቸው የተያዘ መሆኑን በይፋ አሰ ታወቀ። አሁንም አባ ጳውሎስ እንዳይባ ሉ ኦርቶዶክሳዊያን ወገኖቻችንን እናስጠ ነቅቃለን

**ከብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ**

---

# ከበረከተ ወንጌል አምድ

## ክርስቲያናዊ ጋብቻ

«ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም ረዳት የምትሆነውን እንፍጠ ርለት» (ዘፍ. 2፣18)

ጋብቻ ቅዱስና የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ነው። የርኅራሄ አምላክ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለው ዓላማ ፍቅር ነው። ስለሆነም ከሌሎች ሥነ-ፍጥረታት ለይቶ በእርሱ አርአያና ምሳ ሌ ፈጠረው። የሥነ ፍጥረታት ሁሉ ፍጥረታት ሁሉ ተጠቃሚና ገዥ ፤ ተን ከባካቢና ባለቤት አድርጎ ሾመው። «ይጠብቃትና ይንከባከባት ዘንድ የሰው ን ልጅ በኤደን ገነት አስቀመጠው» (ዘ ፍ. 2፣15)

በእግዚአብሔር ዓይን ይህ ሁሉ በቂ ሆኖ አልተገኘም። ለስሙ መቀደሻ ፣ ለክብሩ መውረሻ የፈጠረው የሰው ልጅ ሌላ ያልተሟላለት ነገር ነበር። ይኸም እንደእርሱ ያለ ፣እርሱን መሳይ እርሱን ተመጣጣኝ የኑሮው ተጋሪ የችግ ሩ ተካፋይ ተጋሪ የችግሩ ተካፋይ የሆነ ረዳት ያስፈልገው ነበር።

በመሆኑም ሁሉን ቻይ እግዚአብ ሔር እንዲህ አለ «ሰው ብቻውን ይሆ ን ዘንድ መልካም አይደለም የምትመቸ ውን ረዳት እንፍጠርለት» ከዚህ ቃል እንደምንረዳው እግዚአብሔር አምላክ በእያንዳንዳችን ኑሮ ውስጥ ገብቶ የሚመቸንንና የሚሆነንን እንደሚያስብ ልን ነው። (ፊል. 4፣4-6)

ከዚህ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሀሳ ብና ድንቅ ሥራ በመነሳት ጋብቻን ስን መለከት ጋብቻ ለፍጥረት ሁሉ መገኛ፣ የደስታ ምንጭ፣ የሕይወት ዋልታ በዚ ች ምድር ላይ መለኮታዊ ተቋም ነው። በሌላም አነጋገር የሰው ልጅ ሁሉ ከብ ቸኝነት ኑሮ የሚጠለልበት ብቸኛና አማ ራጭ የሌለው የሕይወት ጎዳና ነው።

ጋብቻ በቤት ሲመሰል የቤቱ ማ እዘኖች ባልና ምስት ሲሆኑ የቤቱ መሠ ረትና ምሰሶ ግን እግዚአብሔር ነው። በመሆኑም ጋብቻ በመንፈሳዊውም ሆነ በአለማዊው ሕይወት ላሉት ሁሉ ታላቅ ሥፍራ አለው። የእያንዳንዱ ሰው ሕይ ወት በቤተሰብ የሚቀረጽና በቤተሰብ የ ሚመሠረት መሆኑን ማንም የሚረዳው ሀቅ ነው።

የቤተሰብ ምንጩ ደግሞ ጋብቻ ነው። ስለዚህ መልካምም ሆነ መጥፎ ቤተሰብ በምንኖረው ህይወታችን ላይ ታላቅ ተጽእኖ አለው። በዓለማችን ዛሬ የምናያቸው ችግሮች ፣ ሥርዓት አልበ ኝነት፣ ልቅነት፣ ውሸት፣ ነፍሰ ገዳይነ ት፣ ጭካኔና አዳዲስ ስልጣኔ መሰል

ሰይጣናዊ ጥበቦች የሰው ልጅ ሰለባ መ ሆኑ የቤተሰብ ጤናማ ያለመሆን (የትዳ ር ብልሹነት) ነው።

ከዚህም አልፎ የሰው ልጅ ዝንባ ሌው በተፈጥሮ በተዋበው በእግዚአብ ሔር ቃል ከተባረከው ቅዱስ ጋብቻ ወ ጥቶ በተዛባ መስመር ተመሳሳይ ጾታን መግባት፣ ትውልድን መሠረት አልባ ማ ድረግ ፣ ከየት መጣሁኝ ፣ ከቤተሰብ ምን ወረስኩኝ የሚለውን ጥያቄ መልስ ማሳጣት ፣ ወደፊት በፋብሪካ የሚመረ ት ትውልድን ማፍራት እንደ ትልቅ ሥ ልጣኔ እየሆነ የመጣበት ዘመን ላይ ነን ። በሌላም በኩል ብዙ ወገኖች እርስ በ ርስ በመፈራራት አንዱ ለአንዱ ታማኝ ባለመሆን ሲያታልል፣ ሲካካድ ይገኛል። የብዙዎች ቤት ፈርሷል፣ የብዙዎች ቤ ተሰብ ተበትኗል፣ የብዙዎች የትዳር ዕ ድል በጨቅላው ተቀጭቷል። ጋብቻ ፍ ቅር መሆኑ ቀርቶ በቀልና መጠፋፋትን አፍርቷል። የሕይወት ጉዞ መሆኑም ቀር ቶ ለአጭር ጊዜ (Part-time) ወይም እ ስከ ከሰዓት ሆኗል።

ሌሎችም እንዲሁ ግራ በመጋባ ት እንደ ደቀ መዛሙርቱ «የባልና የሚ ስት ሕግ እንደዚህ ከሆነ መጋባት ይቅር » እንዲሉ ወይም ቆርጠው ሳይተዉ ወ ይም በመተማመን ሳይገፉበት በመሃል እርስ በርስ የማታለል ጨዋታ እየተጫ ወቱ እድሜአቸው ትቷቸው እየሄደ ያ ሉት እጅግ በጣም ብዙዎች ናቸው። እ ግዚአብሔር ግን ለሁሉም መልስ አለው ና ሰባራውን የሚጠግን፣ የፈረሰውን ትዳ ር ዳግም የሚሠራ፣ እነሆ ጋብቻውንም ፈልገውት ነገር ግን በተለያየ መንገድ ለ ተሰናከለባቸው ወገኖች ሁሉ መፍትሄ ያ ለው እርሱ ነውና ቃሉ ምን ይላል? ይህ ንን ጥያቄ ለመመለስ፣ ማለትም ለጋብቻ ትልቁ እንቅፋት ምንድነው? የባለትዳሮ ቹን ፍቅር በጨቅላነቱ የሚቀጨው፣ የ ወጣቱን ሕይወት ታማኝነት አልባ ያደረ ገው ምን ይሆን የሚለውንና የሁሉን ጥ ያቄ ሊመልስ ይችላል በማለት ክርስቲያ ናዊ ጋብቻን በሦስት አበይት ክፍሎች በመክፈል እንመለከታለን :-

- ቅድመ ጋብቻ
- ከእጮኝነት እስከ ጋብቻ
- ከጋብቻ በኋላ የቤተሰባዊ ሕይወት

## ቅድመ ጋብቻ

### ሀ - ከመተጫጨት በፊት

የጋብቻ ጽናትም ሆነ መፍረስ ከ መሠረቱ ነው። የአንድ ተክል እድገቱና የቁመናው አቅጣጫ የሚወሰነው በአተካ ከሉ ነው። ባለቤቱ ጠመም አድርጎ ተክ ሎት ከሆነ ጠማማ ዛፍ ሆኖ ያድጋል። አስተካክሎ ተክሎት ከሆነ ቀጥ ብሎ ያ ድግና ለብዙ አገልግሎት ይውላል። ጋብ ቻም ትኩረትና ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚ ገባው ከመሠረቱ ላይ ነው በመሆኑም እ ንድ ወጣት ቅድመ ጋብቻ ወይም ከመተ ጫጨት በፊት ማሟላት ያለበት (ያለባ ት) መስፈርቶችና ሊመልሳቸው የሚገቡ ጥያቄዎች አሉ። ከሁሉም በፊት ለትዳ ር የሚዘጋጁ ወጣቶች የአካል ዝግጅት፣ የአእምሮ ብስለት፣የመንፈስ ጥንካሬ ያ ስፈልጋቸዋል። በዘልማድ ዐቅመ አዳም ዐቅመ ሔዋን አድርሷል አድርሳለች እ የተባለ የሚነገረው ይኸው አካላዊ ዝግ ጅት፣ አእምሮአዊ ብስለትና መንፈሳዊ ጥንካሬ ነው። ከዚሁ ጋር የእግዚአብሔ ር ቃል ወደ ማን መሄድ እንዳለብን፣መ ነሻችን ከየት መጀመር እንዳለበት ሲጠ ቁመን እንደዚህ ይላል።

«ቤትና ባለጠግነት ከአባቶች ይወረሳሉ አስተዋይ ሚስት ግን ከእግዚአብሔር ዘ ንድ ናት» (ምሳ. 19፥14)

ከዚህ ላይ የምንረዳው ባልና ሚ ስት እንደ ቤትና ንብረት ከወላጆች አለ

መወረሳቸው ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዘንድመሆናቸው፣ ሊስማሙ፣ ሊመቻቹ፣ ሊረዳዱና ሊቻቻሉ የሚችሉትን ሰዎች እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው ጋብቻ የልብ መግባባትና መመቻቸት ነውና። እ ግዚአብሔር የሁላችንን ባሕርይ ያውቃ ልሰው ግን ሰውን አጥንቶ የሚዘልቅ አ ይደለም የተደበቀ ጠባይ ሁሉ ወደ ኋላ ይገለጣልና። ኀዘንና ደስታን፣ ማግኘትና ማጣትን አብረው አሳልፈው ተካሰው ፍ ርድ ቤት የሚቆሙ ዓይንህን ዓይንሽን ለአፈር የሚባባሉ ክብራቸውን አጥተው ለሌሎች መዘባበቻና መሳለቂያ የሚሆኑ ብዙዎች ናቸው። እንግዲህ ወጣቶች በ ንስሐ ወደ እግዚአብሔር ከመጡ በኋላ በቃሉና በጸሎት እየተጉ የሚመልሷቸው ጥያቄዎች ከዚህ ቀጥለው ያሉት ናቸው።

1. በትዳር ሕይወት ኃላፊነትን መሸ ከም የምችል ሰው ነኝ?
2. ለትዳር ጓደኛዬ ራሴን መስጠት እችላለሁኝ? (1ኛ ቆሮ. 7፥4 ዘፍ. 2፥22)
3. ለትዳሬ መስዋዕት መክፈል እች ላለሁኝ? (ዘፍ. 29፥20)

ክርስቲያናዊ ጋብቻ የልብ መግባባትና እውነተኛ ፍቅር ስለሆነ ከላይ የተጠቀሱ ትን ጥያቄዎች እንድንመልስ ይጠይቃል ። በእውነተኛ ፍቅር የተጣመሩት ባለት ዳሮች እርስ በርስ ለመሸካከምና ለመቻ ቻል ለሚፈጠረው ችግር በራቸውን ሳይ ከፍቱ በአንድነትና በጸሎት በመቋቋም በቅድሚያ ኃላፊነትን መረዳት አለባቸ ው ሌላው የጋብቻ ትክክለኛ ትርጉሙ መሰጣጣት ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለው «ሚስት በራሷ ላይ ሥልጣ ን የላትም ሥልጣን የባልዋ ነው እንጂ፣ ባልበራሱ ላይ ሥልጣን የለውም ሥልጣ ኑ የሚስት ነው እንጂ»(1ኛ ቆሮ.7፥4)ራ ሱንየሰጠ ባል ለሚስቱ ድብቅ አይደለም ራሷን የሰጠች ሚስት ከባልዋ የተለየ አ ንደበትና ጆሮ የላትም። ራስን በመስጠት ላይ የተመሠረተ ትዳር በገንዘብና እጅግ ጥቃቅን በሆኑ ነገሮች አይታወክም፣ ፍቅ ሩም አይቀዘቅዝም። ከዚሁ ሁሉ ጋር ጋ ብቻ መስዋዕት የሚያስከፍል መሆኑን አ ዲስ ተጋቢዎች በቅድሚያ መረዳት ያለ ባቸው ጉዳይ ነው። መስዋዕቱ ምንድነ ው? የሚለውን ጥያቄ በ3ኛው ክፍል እ ንመልሳለን። እዚህ ላይ የተነሳው ግን ትዳር የሚመሠርቱ ወጣቶች በትዳር ሕ ይወት ውስጥ ሊከሰት ለሚችለው ችግር ሁሉ እንግዶች እንዳይሆኑ ከማድረጉም በላይ ችግሮቹን በቅድሚያ አውቀው እ ንዲጸልዩበትና፣ የመንፈስ ቅዱስን ትጥቅ እንዲታጠቁ ለማድረግ ነው።

## ለ - በእጮኝነት ወቅት

ትዳር የሚመሠርቱ ወጣቶች እግ ዚአብሔርን አስፈቅደውና እርሱን ዓይና ቸውና ጆሮአቸው አድርገው የሚወጡበ ት ጊዜ ጥንቃቄ የተሞላበት የትውውቅ ጊዜ ነው። ትውውቅ ወይም መተጫጨ ቱ በተለያዩ ሰዎች ወይም በወላጆች የ ሚመረጥ ወይም የሚጠቆም ይሆናል። ነገር ግን ወሳኙነቱ የሁለቱ ጓደኛሞች ብ ቻ ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስ (በብሉይ ኪዳን) ዘመን ሳኦል ለዳዊት ሜልኮልን፣ ኖኃሚን ለቦኤዝ ሩትን እንደአጩ እናነ ባለን። ይህ አካሄድ በሀገራችንም አያሌ ሰዎች ተጠቅመውበታል አሁንም የሚጠ ቀሙ ይኖራሉ ሆኖም ከሁለቱ እጮኛሞ ች ፈቃድና ውዴታ ውጭ ለዝምድና፣ለ ሥልጣንና ለክብር ተብሎ ስለሚደረግ ጋ ብቻው አብዛኛውን ጊዜ ጤናማ አይሆን ም።

ሌላው በትውውቁ ጊዜ የቀደመ ውን ሥፍራ የሚይዘው ቋሚ መስፈርቶ ች ሲሆኑ እነዚህም :-

1. ኃይማኖት
2. እድሜ
3. በእውቀትና በአስተሳሰብ ተመጣ ጣኝነት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በዚህ ጊዜ አዲሶቹ ተዋዋቂዎች ከራሳቸ ው አልፈው ስለቤተሰባቸው፣ ስለአለፈ

ውና ስለወደፊቱም የሚነጋገሩበት እጅግ በጣም ልዩ የሆነ ጊዜ ነው። ከዚሁ ጋር ሁለቱ የዘለዓለም ሕይወት ጎጆአቸውን ለመሥራት የተነሱ እጮኛሞች በመካከላቸው የዘወትር አጀንዳ አድርገው ወይም እንደማጎተም በአንገታቸው ሊያስሩ የሚገባቸው ነጥቦች አሉ። እነዚህም :-

1. ግልጽነት
2. መተማመን
3. በውሳኔ መጽናት

1. **ግልጽነት** :-

በግልጽነት ላይ የተመሠረተ ጋብቻ ወይም ጓደኝነት በዓለት ላይ የተገነባ ቤት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እምነትና ስለምግባር ጽናት በማቴዎስ 7፥26 የተናገረውን ይመለከታል። የወሬ፣ የሐሜት፣ የቅናት፣ የምቀኝነት ማዕበል ሞገድ ሊፈነቅለው የማይቻለው ጠንካራ ግንብ ነው። ወንዱ ሴቷን ለማሳመን የሌለውን ፀባይ ለማሳየት መሞከር፣ የሌለውን ሀብት መቁጠር፣ የማይዘልቅ ፈገግታን ማሳየት፣ ለስላሳ ድምፅን ማሰማት ግልጽነት ሳይሆን የአደባባይ ድብብቆሽ ነው። የሕይወት ጎጆውንም በአሸዋ ላይና በኮሸሽሌ መሥራት ነው። በውሸትላይ የተመሠረተ ፍቅርም በእንጨት ማሰሮ (ድስት) ወጥ መሥራት ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል በትዳር ጓደኝነት ቀርቶ ከአንድ ልጅ ሁሉ ጋር ውሸትን ማስወገድ፣ እውነትን መነጋገር እንዳለብን ያስጠነቅቀናል። (ኤፌ. 4፥25 ፤ ማቴ. 5፥37)

2 **መተማመን** :-

ሌላው በመተጫጨት ጊዜ ለክርስቲያናዊው ጋብቻ ጎጆ የመሠረት ድንጋይ መሆን ያለበት «መተማመን» ነው። መተማመን ካለ ግልጽነት፣ መተሳሰብ፣ መደጋገፍ ይኖራል። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን በእርሱና በሕዝቡ መካከል ያለውን ግንኙነት በጋብቻ ሲመስለው ወይም እራሱን እንደ ባል ሕዝቡን በሚስት ምሳሌነት ሲያስቀምጥ ዋና የግንኙነት ቁልፍ የሆነው መተማመን መሆኑን እንዲህ ሲል ያስረዳናል። «ለእኔም እንድትሆኚ በመታመን አጭሻለሁ አንቺም እግዚአብሔርን ታውቂያለሽ»(ሆሴ.2፥22)

በአዲስ ኪዳንም በብዙ ሥፍራ ላይ በሙሽራና በሙሽሪት በሚመስለው የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን አንድነት የተቀመጠው ቁልፍ ቃል «እስከ ሞት የታመንክ ሁን»(ራእይ 2፥10)የሚል ነው። በመሆኑም አዲስ ተጋቢዎች ፍቅራቸው እስከ ሞት የጸና እንዲሆን በመተማመን መተጫጨት፣ መዋደድአለባቸው። ከመተማመን የመነጨ ፍቅር ለዘለዓለም አይወድቅም። 1.ቆሮ.13፥8

3 **በውሳኔ መጽናት** :-

በዘመናችን ትዳር የሚመሠርቱ ሰዎች ትልቁ ችግራቸው በውሳኔአቸው አለ መጽናት ነው።በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ያልተመሠረተ ባል ወይም ሚስት ፍለጋ ማለቂያ የሌለው ጉዞ፣ መቋጫ የሌለው ነገር ነው። ምክንያቱም የአንደበት መተጫጨት እንጂ የልብ ውሳኔ ስለአልሆነ ጉዞው ሁሉ በምኞት ተንጠልጥሎ ይቀራል።ይህም የልጅነት ጠባይ ነው። ልጆች ሰው የያዘው ሁሉ ስለሚያምራቸው የያዙትን ጥለው ሌላ ይፈልጋሉ።

አዲስ ትዳር መሥራቾች በመረጡትና በያዙት ላይ መጽናት ይኖርባቸዋል። የልጅነትንም ጠባይ ሽረው በበሰለ አእምሮ ጎጆአቸውን ሊመሰርቱ ይገባቸዋል። (1.ቆሮ. 13፥11)

## ከእጮኝነት እስከ ጋብቻ

### ሀ - በቃል ኪዳኑ ቀለበት መጽናት

ከእግዚአብሔር ቤት ትዳራቸውን የጀመሩ ወጣቶች፣ በነፃ ፈቃዳቸው ተዋ

ደው የተጫጩ፣ በአበ ነፍሳቸው በኩል የንስሐና የጋብቻ እንዲሁም የቅዱስ ቁርባንና የሥርዓተ ተክሊልን ትምህርት የተማሩ ምርጫቸውንና ውሳኔአቸውን በ ቀለበት ቃል ኪዳን ያስራሉ፤ ያትማሉ። ቀለበቱ እርሷ የእርሱ እርሱም የእርሷ መሆኑን የሚያመለክት የውሳኔ ምልክት ነው። በሌላ መልኩም አንዱ በአንዱ መስጠትን የሚያበስር፣ አንዱ በአንዱ ሕይወት ያለ የሚኖር መሆኑን የሚገልጽ ነው። ቀለበት ስሙ እንደሚገልጸው መ ውጫ (Exit)ወይም መግቢያ(Entrance) የለውም። ስለዚህ ቀለበት የውሳኔ ምል ክት ስለሆነ በእርሱ መጠበቅና መጽናት ይገባል። ወጣቶቹ በቃል ኪዳናቸውና በ ውሳኔአቸው እንዳይጸኑ የሚያደርጉ እን ቅፋቶች ለማስወገድ ቁልፍ የሆኑትን ነገ ሮች ከዚህ በታች መመልከቱ ተገቢ ነው።

1. **<u>በፈተና መጽናት</u> (ያዕ. 1፥12)**

በጋብቻ ዙሪያ ፈተና ከውስጥ ከ ሁለቱ ከራሳቸው ሕይወት ከውጭ ከተለ ያየ አቅጣጫ የሚመጣ ፈተና ነው። ከ ሁለቱም አቅጣጫ የሚመጣ ፈተና ገና በጨቅላ ላለው የጋብቻ ሕይወት ከፍተ ኛ አደጋ ስለሆነ ሁለቱም ትኩረት ሊሰ ጡት የሚገባ ጉዳይ ነው።

<u>የውስጥ ፈተና፣</u> ከውስጥ የሚመጣው ፈ ተና የሚገለጥባቸው ነገሮች አለመግባባ ት፣ አለመደማመጥእልከኝነት ፣ አውቃ ለሁ ባይነት ፤ እውር ቅናት ድብብቆሽ ናቸው። ከውስጥ ለሚመጣ ስሜትም ሆ ነፍላጎት መደማመጥ አማራጭ የሌለው መድኃኒት ነው። መደማመጥ ካለም መ ግባባት ይኖራል። የእግዚአብሔር ቃል ም «ሰውሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመና ገር የዘገየይሁን» (ያዕ.1፥19) የሚለው እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው። አንደኛው አካል እኔ ባይነት (እኔ) ብቻ አውቃለሁ የሚል ከሆነ ትዳሩ የንዝንዝ የንትርክ መድረክ፣የሁከትና የሽብር መናኸሪያ መ ሆኑ አይቀሬ ነው። እናስታውስ ታላቁ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ከነዓን ሳይገባ በምድ ረ በዳ የቀረው «እኔ» በማለቱ ነበር (ዘጸ.17፥5-7፣ ዘዳ.32፥51)

ስለዚህ እኔ ባይነት ለፈተና የሚ ያጋልጥና ፍቅርን የሚያጨልም የውስጥ ክፉ ስሜት ስለሆነ ይታሰብበት ዘንድ ይ ገባል።

<u>ከውጭ የሚመጣ ፈተና፣</u>

ከውጭ የሚመጡ ፈተናዎች በ ሦስተኛ አካል የሚፈጠሩና እንዲሁም በገንዘብ በሥራ ወዘተ የሚከሰቱ ናቸው:- አብዛኛውን ጊዜ ግን:-

- ከወላጆች(ከቤተሰብ)
- ከወዳጆች
- ከጓደኞች
- ከሥራ በልደረቦች
- ከጐረቤቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

በእነዚህ ምክንያት የስንቶቹ ቤት ፈርሷ ል፣ ቤተሰብ ተበትኗል፣ የሰንቶቹስ ነባር ፍቅር ቀዝቅዟል። ይህን በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል እንደዚህ ይላል። «አሥግሩ ለነ ቈናጽለ እለ ያማስኑ ዐፀ ደ ወይንነ»«የወይናችንን ቦታ የሚያ በላሹትን ጥቃቅን ቀበሮዎች አጥምዳች ሁ ያዙ» (መኃ.2፥5) በቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተውን ፍቅርንና ግልጽነት የተ ሞላበት መተማመንን ወጥመድ ዘርግተን የወይናችን ቦታ ትዳራችንን፣ ፍቅራችንን አንድነታችንን ሊያበላሹ ሾልከው የሚገ ቡትን ጥቃቅን ቀበሮዎች ወሬኞች፣ሐሰተ ኞች፣ በክፋትና በተንኮል የተሞሉትን ል ንለያቸውና በማሳፈር ልንመልሳቸው ይገ ባል። በአማኞችና በእውነት ተናጋሪዎች ጀርባ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳለ ሁሉ በውሸተኞች ፤ የሌላውን ትዳር ለማፍረስ ፣ ለመለያየት ክፋትን ታጥቀ ው በሚሰለፋት ጀርባ ሰይጣን እንዳለ እናውቃለን ምክንያቱም እርሱ የሐሰት አባት ነውና።(ዮሐ. 8፥44)

ስለዚህ ጌታ «አንተ ሰይጣን ከኋላዬ ዞር በል»ማቴ.16፥23 እንዳለ በአንዲትፍ ቅር የተሳሰሩ እጮኛማዎች የሰይጣን ግ ብረ አበሮች ዞር በሉ ሊሉ ይገባል።

## 2) ፈተና የሚጠይቀውን መስዋዕት መክፈል

ከላይ እንደተመለከትነው ከው ጭም ሆነ ከውስጥ የሚመጡትን ፈተና ዎች ለመቋቋም መስዋዕት መክፈልን ይ ጠይቃል። የይስሐቅ ልጅ ያዕቆብ የአጐ ቱን ልጅ ራሔልን ለማግባት በፈለገ ጊ ዜ ሰባት ዓመት ለአባቷ እንዲገዛ ሲጠየ ቅ በእሽታ ተቀበለ ላባም ጊዜው ሲፈጸ ም ልያን ሰጠው ያዕቆብ ግን የወደዳት ራሔል ስለሆነች ራሔልን ደግሞ ለማግ ኘት ሌላ ሰባት ዓመት መገዛት ነበረበት ሆኖም ፍቅር ነውና የሚገባውን መሰዋዕ ት ከፈለ። (ዘፍ 29፥18 - 30)

## ለ) ጋብቻ በተዋኅዶ ምሥጢር ሲመሰል

በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ የእርሱንና የሕዝቡን ግኑኝነት በባልና በሚስት፣ በሠርግ ቤት፣ በሙሽ ራና በሙሽሪት ፤ በሠርገኞችና በታዳሚ ዎች መስሎ በነቢያት በሐዋርያት ያጻፈ ውን ምሳሌዎች እናነባለን፤ ይህም የሚ ያሳየው የጋብቻውን ክቡርነትና ታላቅነት ነው።

- በባልና በሚስት (እግዚአብሔርና እስራኤል) ሆሴ.2፥22፤ኤር.3፥14
- በሙሽሪትና በሙሽራ (ክርስቶስ ና ቤተ ክርስቲያን) መኃ.2፥5፣ ዮሐ 3፥25፣ ማቴ 9፥15፣25፥1፣ 1ኛ ቆሮ. 11፥2፤ ኤፌ.5፥23-31
- በሠርግ ቤት (የእግዚአብሔር መንግሥት፣ ቤተ ክርስቲያን) ማቴ. 22፥1-10፣ ራዕ 19፥7-9

ከላይ ከተቀመጡት ጥቅሶች መካከል ጋ ብቻን በተዋኅዶ ምሥጢር የሚገልጸውን የኤፌሶንን መልእክት እንመልከት። በዚህ ክፍል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ዓረፍተ ነገሩን ሲዘጋ «ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው እኔ ግን ይህንን ስለክርስቶስ ና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላላሁ» (ኤፌ 5፥32) ይላል።

የክርስቲያናዊ ጋብቻን ሥርዓትና አፈጻጸም በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን አንድነት ማነጻጸሩ ምንኛ ድንቅ ነው። ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ስትወለድ ም ሥጢር እንደሆነ ሁሉ የባልና ሚስትም አንድ ሥጋ መሆን ምሥጢር ነው። ይህንን «ታላቅ ምሥጢር» የተባለውን በዝርዝር ለማየት አመች ይሆን ዘንድ ለሁለት እንከፍለዋለን።

## 1) የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ መሆኑ

### ሀ. ዘለዓለማዊ ፍቅር

«ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤ ተ ክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻች ሁን ውደዱ» ቁ.26 ይህም ማለት ክርስ ቶስ ቤተ ክርስቲያንን የወደደበት ፍቅር ማለት ነው። ይህም ታላቁን የእግዚአብ ሔርን ፍቅር ይገልጸል፣ የእርሱ ፍቅር መነሻ መድረሻ የለውም ዘለዓለማዊ ነ ው እኛ የሰጠነው ነገር ለእርሱ መነሻ የሁነው ከቶ ምንም ነገር የለም።(ዮሐ. 3፥16) እንዲሁ ወደደን ስለዚህም እኛን ሆነ ከኃጢአት በስተቀር ከኛ ጋር ተባበ ረ በሁሉም ተካፈለ። ዕብ 2፥15-16፣ 4፥ 15 እኛን ስለሆነ እኛን ወንድማቼ፣ እህ ቶቼ ወዳጆቼ ለማለት አላፈረብንም። ( ዕብ 2፥17፣ 13 ዮሐ. 17፥28፣29 ማቴ 1 1፥50)

ባሎችም እንዲሁ ለሚስቶቻቸው ያላቸው ፍቅር በገንዘብ የሚለካ፣ በጥቃ ቅን ነገር የሚመዘን መሆን የለበትም። ጋብቻ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን ወህ ደት ሲነጻጸር አንዱ ለአንዱ መሰጠትን ያስተምረናልና። ቤተ ክርስቲያን በዘለዓ ለማዊ ፍቅር ለወደደት (ዮሐ.13፥1) ክር ስቶስ ትገዛለች፣ ትታዘዛዋለችም የክርስ ቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን የ

ተመሰለችው ሚስትም ለባልዋ ትታዘዘዋ ለች። «ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስ ቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ» ይህ ማለት ብዙዎች እንደሚያስቡት የሚስት የበታችነትን፣ ጭቆናን፣ ልዩነትን የሚያስተምር ማለት አይደለም። የፍቅር መገዛት፣ የፍቅር መታዘዝ ነው እንጂ። የእግዚአብሔር ቃልም እንደሚነግረን የሚጨቁናትን ሚስት አገኘ ሳይሆን «ሚስት ያገኘ በረከት አገኘ» ነው የሚለው(ምሳ 18፥22) በበረከት መራብ፣ በፍቅር መናናቅ የለምና። በተፈጥሮም እግዚአብሔር ሴትን ለመፍጠር አንዲት አጥንትን ከአዳም በወሰደ ጊዜ ከእግሩ አልነበረም የበታችኝነት እንዲሰማት ወይም ከራሱ ላይም አልነበረም የበላይነት እንዲሰማት ነገር ግን ከጐኑ ነበር። ጐን እኩልነትን፣ መረዳዳትንና መተጋገዝን ያስረዳል ማንም በዚህ ዓለም ወዳጁን ከጐንህ እቆማለሁ ነው እንጂ ከራስ ወይም ከእግር አይደለም የሚለው። ይህን ያደረገ፣ እግዚአብሔር ይመስገን። አሜን!

ለ. <u>እራስን አሳልፎ መስጠት</u>

ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን መውደዱ ብቻ አይደለም እርስዋ ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ራሱን አሳልፎ ሰጠ ስለ እርስዋ በአደባባይ ተንገላታ፣ተገረፈ ተዋረደ (ቁ.26፥27) ባልም እንዲሁ ለወደዳትና አካሉ ለሆነችው ሚስቱ ጀርባውን ሳይሆን እስከሞት ድረስ ራሱን አሳልፎ የሚሰጣት ለፍቅርዋ የሚገዛ ሊሆን ይገባል።(ቁ. 33)

## 2) <u>ጋብቻ በሥርዓተ ተክሊል</u>

ክርስቲያናዊ ጋብቻን ልዩ የሚያደርገው ቤተ ክርስቲያን በሥርዓተ ተክሊል፣ በልዩ ጸሎትና ዝማሬ የምታከብረው በመሆኑ ነው። በምሥጢረ ተክሊል ውስጥ የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ መተላለፊያዎች የሆኑ ንዋዬ ቅዱሳቶች አሉ። እነዚህም:-

- ቀለበቶች
- ካባዎች
- ቅብዐ ቅዱስ
- አክሊሎች ናቸው።

እነዚህ ንዋየ ቅድሳት እያንዳዳቸው የተለየ ጸሎት የሚጸለይባቸው ሲሆኑ የጸሎቱ ዋና ዓለማ መንፈስ ቅዱስ አዲሶቹን ሙሽሮች በዘለዓለም ፍቅር እንዲያዋህዳቸው ነው። ከእግዚአብሔር ቤት መነሻውን ያደረገ ጋብቻ በእግዚአብሔር ቤት ይፈጸማልና። በዚህ ጊዜ ጌታ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ተገኝቶ ጋብቻውን እንደባረከ ፤ ችግራቸውንም እንዳስወገደላቸው በጎደለውም በረከቱን እንዳፈሰሰ ዛሬም በአማኙ ሰርግ እርሱን የሚወክለው ሊቀጳጳሱ (ካህኑ) የእርሱን በረከት ያስተላልፋል። ይህም የተክሊል ሥርዓት በመጀመሪያ ለሚጋቡት ሁሉ የሚፈጸምላቸው የበረከት አገልግሎት ነው።

ዮሐ 2፥1-11

**ይቀጥላል**

**መልአከ ሰላም አባ ቃለጽድቅ**

---

# <u>ሕገ እግዚአብሔር</u>

ሕግ ከማንም በላይ የሆነ ሁሉም የሚመራበት ነው። ፍጥረት ሁሉ ግእዛን አዕምሮ ያለውም የሌለውም የሚመራ በተፈጥሮ ሕግ ነው። ስዎችም በመጀ

መሪያ ጊዜ የሚሄዱት የሚሠሩት በጠቅ
ላላው የሚኖሩት በሕገ ልቦና በተፈጥሮ
ሕግ ነበር። እየቆየ ግን የጽሑፍ ሕግ
አስፈለገና እግዚአብሔር አምላክ ለሰ
ው ልጅ የጽሑፍ ሕግን ሠራ እሱም
በእጁ ጽፎ በራእይም በልዩ ልዩ ክስተ
ትም እየተናገረ በሙሴ አማካይነት የብ
ሉይ ኪዳንን ሕግ አጸፈ።

በፍጻሜ ዘመን ደግሞ ለአዲሱ
እስራኤል አዲስ ሕግን፣ ሕገ ወንጌልን
ሠራ። በጠቅላላው ለሰው ልጅ ሕግ
ይሆን ዘንድ በማያዳግም መልክ ሕገ
ወንጌልን ሠራ።

በመሠረቱ ሕግ ማለት ሁሉን
በትክክል የሚያስኬድ፣ የሚመራ
የሁሉም እርምጃ ትክክለኛ መሆኑን
የሚመዝን ነገር ነው፣ በተለይ ኅብረተ
ሰብን፣ ማኅበርን የሚያገናኝ አንድ
የሚያደርግ ሁሉም እኩል መሆናቸውን
በስምምነት መሄድ እንደሚገባቸው
የሚያመለክት ሚዛን ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም
በብሉይ ኪዳን ልዩ የሆነ የሕግ መልክ
ታይቷል። ይኸም ሕግ የእግዚአብሔር
ወገን የተባለው የእስራኤል ወገን ልዩ
ሕዝብ ስለሆነ በሕገ ወጥነት እንዲኖሩ
እግዚአብሔር አልፈቀደም። ከአምላካ
ቸው ጋር ለሚያገናኛቸው አምልኮተ
ሕግ ሠራላቸው እንዲሁም እርስ በራሳ
ቸው በስምምነት በአንድነት እንዴት እ
ንደሚሄዱ፤ እንዴት እንደሚኖሩ የሚያ
መለክት ሕግ ሠራላቸው። በዚህም አም
ላካዊ ሕግ የእስራኤል ሕዝብ ይመራና
ሥነ-ሥርዓትም ጠብቆ ይሄድ ነበር።

ሕግ የተጠበቀውን ያህል የሰው
ም ሕይወት ይጠበቃል፤ ሕግ የፈረሰውን
ያህል ደግሞ ሕዝብ ጸጥታ ያጣል ኑሮ
ው ይመሰቃቀላል፣ ሕብረት አንድነት
ይጠፋል።

እስራኤል ከእግዚአብሔር የተቀ
በሉትን ሕግ አክብረውና ጠብቀው በመ
ኖራቸው ሕዝበ እግዚአብሔር ያሰኛቸ
ው ነበር። ሕግ ያልነበራቸው አሕዛብ
ግን አሕዛብ፣ አረሚ እየተባሉ ይጠሩ
ነበር፣ ይሁን እንጂ ዓለም በሕግ መሄድ
ግድ ስላለበት ቋሚ አይሁን እንጂ ለራ
ሳቸው አሕዛበ ሕግ ነበራቸው። ማንም
ያለ ሕግ ሊኖር ሰለማይችል የሕግ ሉዓ
ላዊነት ይታወቅ ዘንድ አሕዛብም ሕግ
እንደነበራቸው እንረዳለን። ስለ አሕዝ
ብ ሕግ ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጥ «ሕግ
የሌላቸው አሕዛብ ከባህሪያቸው ሕግ
ሲያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው
ለራሳቸው ሕግ ናቸው። ሕግን ማድረግን
ይገልጣሉ በልባቸው የተጻፈውን» ሲል
ይነግረናል። (ሮሜ ፪፥፲፬ - ፲፭)

አሁንም የሙሴ ሕግ ወይም ሕገ
እግዚአብሔር የተባለው ከአሕዛብ ሕግ
በብዙ መልኩ ይለያል፣ ማለት፦

1 - የአሕዛብ ሕግ ሰው ሰራሽ
እንደመሆኑ ሁሉን አያሟላም፣

2 - የአሕዛብ ሕግ የየዘመኑ
መሪዎች በእነርሱ ፍላጎት ብቻ የተሠራ
በመሆኑ ይህኛው አልፎ ያኛው ሲተካ
አዲሱ መሪ የነበረውን ሕግ ይሽረዋል፤
እርሱም ለራሱ የሚሆነውን ሕግ ይሠራ
ል፣ በዚህ መልክ ሲለዋወጥ የኖረ እን
ጂ ቋሚ ሕግ ሊኖራቸው አልቻለም።

ሕገ እግዚአብሔር ወይም የእስ
ራኤል ሕግ ግን መጀመሪያውኑ እግዚአ
ብሔር አምላክ ጽፎ አጽፎም የሰጠው
ሰለሆነ የዘለዓለም ሕግ ነበር። ክርስቶስ
ም ሲያስተምር ሰማይና ምድር እስኪያ
ልፉ ድረስ የወጣ አንዲቱ ወይም ጽህፈ
ቴ ከኦሪት (ከሕግ) አታልፍም ሁሉ እሰ
ኪሆን እያለ መስክሯል (ማቴ ፭፥፲፰)

ይህ አምላካዊ ሕግ እስራኤልን
ከአምላካቸው ጋር እስራኤላዊያንንም
እርስ በራሳቸው አገናኝቶ አስተሳስሮ
የኖረ ነው።

እግዚአብሔርም ሕግ አውጥቶ
ለሰው መስጠቱ የፍቅር ምልክት ነው፤
ማለት እያንዳንዱ ከአምላኩ ርቆ እንዳ
ይኖር፣ ወይም ሕዝብ እርስ በርሱ ተለ
ያይቶ እንዳይኖር እንደ አንድ ቃል ተና
ጋሪ እንደ አንድ ልብ መካሪ ሆኖ ትል

ቅ ሕዝብ ሆኖ የኖረ የሚኖር አድርጎታል። የሕግ ሉዓላዊነትም ይህን የመሰለ ነው፣ ማለት እስራኤላዊያን ሕግን ጠብቀው ሕጋውያን ሆነው ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት አግኝተው ሲኖሩ፣ እግዚአብሔር አምላክም ሕዝበ እስራኤልን ሞገሰ ሰጥቶ ክብር ሰጥቶ የተለዩ ወገኖች ወይም የእርሱ ወገኖች አድርጓቸው ይኖራልና።

ይኸም ሕግ ቀድሞ ለእስራኤል ብቻ እንደሆነ ይነገር ነበር። ክርሰቶስ በዚህ ዓለም ሲገለጥ ግን የእግዚአብሔር ሕግ እንደመሆኑ ለአዲሱ እስራኤል፤ ወይም ለእስራኤል ዘነፍስ የተሰጠ ሆነ ከሐዲሱ ኪዳን ሕግ ጋራም ተባበረ።

አሁን የእግዚአብሔር ሕግ የሰውን ልጅ ወደተሻለ የኑሮ ደረጃ የሚያደርስ የሞራል ሕግ ሁኖ ይሠራል። በመጀመሪያ አሁንም ወደ እግዚአብሔር አምላክ መርቶ ያደርሳል፤ የመጣበትን ዓላማ የመጣበትን ተልእኮ ገልጦ ያስረዳል።

«እኔ በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛል» ሲል ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ሊለኝ የእግዚአብሔርም ሕግ ልንጠብቅ ይገባናል (ሮሜ ፯፥፳፪)።

እግዚአብሔር አምላክ በሙሴ አማካይነት የሠራው የተናገረው ብዙ ነው፤ ያንን ሁሉ ሰዎች የመጠበቅ የማክበር ግዴታ አለባቸው፤ የተጻፈው ሁሉ ለኛ መመሪያ ነውና። ቅድስ ጳውሎስም «አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ እኛን ለማስተማር ተጽፏልና ተስፋ ይሆንልን ዘንድ በትዕግሥት በመጸሕፍትም በመጽናናት» (ሮሜ ፲፫፥፬)

በሕግ መልክ የተጻፉ አምስቱ የሙሴ መጽሐፍ ሐዲስ ኪዳን በመላ ናቸው፣ እነዚህን የሰው ልጅ ቢጠብቅ ከአምላክ ጋር ያለው ግንኙነት ፍቅሩም ይገለጣል «የሚወደኝ ሕጌን ይጠብቅ» ይላልና (ዮሐ. ፲፬፥፲፭)።

የአምላክ ሕግ አምላክ ከሰው ፍጹም ፍቅር የተነሳ የተሠራ ነው፤ የሰው ሕግ ጠባቂነትም ከእግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር የተነሳ ነው። « ትእዛዜ ወደእርሱ ያለች የሚጠብቃትም ያ ነው የሚወደኝ። የሚወደኝም አባቴ ይወደዋል፣ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጥለታለሁ» ሲል ክርስቶስ ያስተምረናል (ዮሐ. ፲፬፥፳፩)። እንግዲያውስ ፍፁም ፍቅር በአምላካችን ላይ ይኑረን፤ መገለጫውም ሕጉን በመጠበቅ ይሁን።

**ከብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ**

---

# <u>እኔ ማን ነኝ</u>?

ብዙ ጊዜ እኔ ማን ነኝ? ምን እየሰራሁ ነው? ከየት ተነሳሁ? የት ደረስኩ? ወዴት እየሄድኩ ነው? ያልንበት ጊዜ ሁላችንም ብናስብ መኖሩ አጠራጣሪ ነው። በዚህ ፈንታ እገሌ ማን ነው? ምን ይሰራል? እንዲህ ነው እንዲህ አይደለም እያልን ስለባልንጀራችን ከዚያም አልፎ ስለማናውቀው ሰው ያወራንበት የተረክንበት ጊዜ ግን መጠን የለውም። ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ የሰው ልጅ እኔ ማን ነኝ? ብሎ ራሱን መመርመርና መፈተን እንደሚገባው ሲያስረዳ፥ "በኃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ ራሳችሁን ፈትኑ" 2ኛ. ቆሮ. 13፥5

እኔ ማን ነኝ? ማለትም በስም፣በ ሥራ፣ በሐሳብ፣ በአካሄድ፣ በአጠቃላይ በሕይወት ሁሉ ነው ብዙ ሰዎች "አንተ ማን ነህ" ተብለው ሲጠየቁ በቀጥታ ልባ ቸው ውስጥ የሚገኘው መልስ ስሜ እገ ሌ ነው የሚለውን ሳይሆን እንደማይቀር እንገምታለን። ሆኖም ግን አንድ ሰው ይህን ጥያቄ ሲጠየቅ መመለስ ያለበት ስሙን ብቻ ሳይሆን ኃይማኖቱን፣ ሥራ ውን፣ እንቅስቃሴውንም መላ ሕይወቱን በማገናዘብ ሊመልስ ይገባዋል።ያለበለዚ ያ ግን ያ ሰው መልሱን በሙሉ መለሰ ለማለት አስቸጋሪ ነው።

ለመሆኑ በዚህ ውጣ ውረድ በሰፈነ በት ዓለም አለመተማመን ጎልቶ በሚታይ በት፣ ፍቅር ጨርሶ በቀዘቀዘበት ዘመን ች ግርና ረሀብ በሽታና እርዛት ለሰው ልጆች የቅርብ ዘመድ በሆኑበት በዚህ ጊዜ የምገ ኝ እኔ ማን ነኝ? እኔ እኮ! ኃጢአት በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ሳይሰለጥን ጥንት ያን ጊዜ ክብር የነበረኝ እኔን መሰሉ የሰው ል ጅ ይቅርና አራዊትና እንስሳት እንኳን ይ ገዙልኝ የነበረ ችግርና ረሀብ ኃዘንና ለቅሶ በተግባር ይቅርና በልብ እንኳን የማይታሰ ቡበት የደስታ ወንዝ ይፈስበት የነበረ ኑሮ ተሰጥቶኝ የነበርኩ ነገር ግን በእምነት አጉዳይነቴና አልታዘዝ ባይነቴ ያ ሁሉ ጸ ጋ የተወሰደብኝ ሰው ነኝ ይገባኛል ቅጣት ዘፍ. 3፥7-8

እኔ እኮ እግዚአብሔር አምላክ መልካም ነው ሲለኝ ክፉ፤ ጣፋጭ ነው ሲለኝ መራራ ሆኜ የተገኘሁ አሳዛኝ ፍጥረ ት ነኝ ከክብር ይልቅ ውርደት፣ ከደስታ ይልቅ ኃዘን፣ ከሕይወት ይልቅ ሞትን መ ርጬ ወደዚህ ዓለም የመጣሁ ነኝ። የእኔ አንሶ ግዑዟ ፍጥረት ምድር እንኳን እሾ ህና አሜኬላ ታበቅል ዘንድ ያስረገምኩ አሳዛኝ ፍጥረት ነኝ። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን እግዚአብሔር ራሱ ፍቅር ስለሆነ ያለምን ም አስገዳጅ ይወደኝና ያፈቅረኝ ነበር። ዘፍ. 3፥17

እግዚአብሔር በተለያየ ክፍለ ዘመ ናትም ትዕዛዜን ጠብቅ ብልህ ያልጠበቅህ ከእኔ ይልቅ ራስህን ያስቀደምክ ፍጥረት ነህና ከአንተ ጋር ምንም ግንኙነት ሊኖረኝ አይገባኝም ብሎ ያልተወኝና ቸል ያላለኝ ልዑል እግዚአብሔር ድምፁን እያሰማ ራ ሱን የገለጠ በሕልም በራዕይ በነቢያትና በቅዱሳን አባቶች ሲያጽናናኝ የኖርኩ ዕድ ለኛ ፍጥረት ነኝ።ዘፍ.28፥12-17፣ኢሳ.40፥1

ይልቁንም የሚወደኝና የሚያፈቅረኝ ጌታ መሆኑን ለመግለጽ በመጨረሻው ዘመን የእኔን ባሕርይ ባሕርዩ አድርጎ ተወለደ እስ ከ ሞትም ድረስ አፈቀረኝ ፍቅሩንም በሌላ ስጦታ ሳይሆን በደሙ ፈሳሽነት ገለጸልኝ። (ዮሐ. 3፥16 ኢሳ. 53፥1 1ኛ ዮሐ.4፥10)

በድዬ ኃጢአት ሰርቼ ከእርሱ ተለ ይቼ ወድቄ ንስሐ የሚባል የዕርቅ መንገድ ሰጥቶኝ ሥጋውና ደሙን ተቀብዬ የመንግ ሥቱ ወራሽ አደረገኝ።

(ኢሳ.1፥18 1ኛ ቆሮ. 11፥28)

በዚህ ዘመን ያለህ ሰው ሆይ! እኔ ንፁህ የእግዚአብሔር ተክል ነኝ የበቀልኩ ትም ውሃ ጠጥቼ ሳይሆን በቀራንዮ የፈሰ ሰውን ደም ነው። ያለፉት ቅዱሳን አባቶ ች የፈሰሰውን ንፁህ ደም በደማቸው ክሰ ው ተጋድሎአቸውን ፈጽመው ኃይማኖታ ቸውን ጠብቀው አልፈዋል። ታዲያ እኔም ተመሳሳይ እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሥራ ይጠበቅብኛል። እግዚአብሔር አም ላካችን እስከ ሞት ድረስ የወደደኝ፣ በጸ ሎት፣ በጾም፣ በቅድስናና በንጽሕና ያጌጠ ልቦና እንዲኖረኝ እርሱን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ኖሮኝ ለመንግሥቱ እንድበቃ ነው።

ለመሆኑ እኔ ዛሬ ማን ነኝ? ማንንስ ሆኜ ተገኝቼአለሁ? ምንስ እየሠራሁ ነው? ማንንስ ደስ በማሰኘት ላይ ነኝ? ራሴን ወ ይስ እግዚአብሔርን? በውኑ እግዚአብሔር አምላክ ያላደረገልኝ ነገር፣ ያልሰራልኝ የ ሕይወት መንገድ፣ ያላሳየኝ የፍቅርና የወ ዳጅነት ሥራ አለ? በጋና ክረምትን፣ መዓ ልትና ሌሊትን እያፈራረቀ ዓለሙን የሚ መግብ ጌታ ለእኔ የነፈገኝ ነገር ምን አለ? እስቲ ራሴን ልመርምር ልፈትንና እኔ ማ ን ነኝ ልበል።

እኔ ማን ነኝ ብሎ ራሰን የማይመረምር ሁሉ በሕይወቱ ባዶ ነው። እንግዲህ በ ኃይማኖታችን ራሳችንን በመመርመር የምን ጓዝ ከሆነ ዲያብሎስን እናሳፍረዋለን፤ በወንጌሉ ቃል ገስፀን በመጣበት መንገድ እንመልሰዋለን፤ እንዲህ ከሆነ የእግዚአብሔር የ ሚስጥር መጋቢዎች እንሆናለን።

ልዑል እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን! አሜን!

ቆሞስ አባ ፍሬ ሃይማኖት

---

# ይህም በእግዚአብሔር ዓይን ቀላል ነው።

2ነገ 3፥18

እግዚአብሔር አምላክ ዓለምንና መላዋን ሲፈጥር አጋዥ ወይም አማካሪ አላስፈለገውም። የሚታዩትን ሆነ የማይ ታዩትን ፍጥረታት ካለመኖር ወደ መኖር ሲያመጣ ያቃተውና ያሰቸገረው ነገር የ ለም። እንግዲህ ታላላቅ ፍጥረታትን ብ ቻውን ያስገኘና የፈጠራቸውን ዓለማትን በእጁ መደፍ የያዘ ጌታ የገዛ ፍጥረቱን እንደፈለገ ማድረግና ማዘዝ ያስቸግረዋልን?

በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ምዕ 3፥ 5-20 ላይ የተጻፈ አንድ ታሪክ አለ። ይ ኸውም ቤተ እስራኤል ለሁለት በተከፈለበት ወቅትና የኤልያስ መንፈስ በኤል ሳእ ላይ እጥፍ ድርብ ሆኖ በወረደበት ጊዜ የእስራኤል ንጉሥ ኢዮራም ግብር አልገብርም ብሎ በርሱ ላይ ያመፀውን የሞአብን ንጉሥ ሊወጋ ፈለገ። በስልፋ ላይ ያግዘውም ዘንድ ወደ ይሁዳንጉስ ኢዮሳፍጥ ላከበት። በዚህ ጊዜ የይሁዳ ንጉስ፣ የእስራኤል ንጉሥ፣ የኤዶምያስ ንጉሥ ሆነው ሞአባውያንን ለመውጋት በኤዶምያስ ምድረ በዳ እየሄዱ ሳለ ት ልቅ ችግር ገጠማቸው። እነሆ እነርሱ ከብቶቻቸው፣ ሰራዊቶቻቸው ሁሉ የሚ ጠጡት ውሃ አጥተው በውሃ ጥም ሊያ ልቁ ሆነ። የእስራኤል ንጉሥም፣ «ወዮ! እግዚአብሔር በሞአብ እጅ አሳልፎ ይ ሰጠን ዘንድ ጠርቶናልና ወዮ!» አለ የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሳፍጥ ግን «በእርሱ እ ግዚአብሔር የምንጠይቅበት የእግዚአብ ሔር ነቢይ በዚህ አይገኝምን?» አለ። በዚህ ጊዜ ከኢዮራም ባርያዎች አንዱ የኤልያስ ደቀ መዝሙር ኤልሳእ በዚህ አለ ሲል ተናገረ ። ኢዮሳፍጥም «የእግ ዚአብሔር ቃል በርሱ ዘንድ ይገኛል» ሲል ሁለቱን ነገሥታት ይዞ ወደ ነቢዩ ዘንድ ሄደ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በኤልሳእ ላይ አድሮ ተናገረ። እንዲህ ም አለ፦ «በዚህ ሸለቆ ሁሉ ጉድጋድ ቆፍሩ .... ንፋስ አታዩም፣ ዝናብም አታ ዩም፣ ይህ ሸለቆ ግን ውሃ ይሞላል። እ ናንተም ከብቶቻችሁም ትጠጣላችሁ ይ ህም በእግዚአብሔር ዓይን ቀላል ነገር ነው። ሞአባውያንንም በእጃችሁ አሳል ፌ እሰጣለሁ» አለ እንደተናገረም በነጋ ው የቁርባን ጊዜ ሲደርስ በኤዶምያስ መንገድ ውኃ መጣ ሰልፋም ተከናወነላ ቸው። ክብር ለእርሱ ይሁን።

አንባቢያን! እኛ የታመንበት አም ላክ ይህ የቅተዋል የሚባልለት አይደለ ም። ለእኛ ለሰዎች ከአዕምሮ በላይ ሆ ኖ ያስጨነቀንና ተስፋ ያስቆረጠን ነገር ለርሱ ምንም ነው። ነቢዩ ኢሳያስ «ድን ቅ መካር» ሲል የተናገረለት ጌታ በባህ ር ላይ የሚራመድ፣ ነፋሳት የሚታዘዙለ ት፣ እጅ በምታህል ደመና ምድርን በው ሃ የሚያረሰርስ፣ ውሃን እንደ ግድግዳ የ

ሚያቆም፣ ውሃን ከዓለት ላይ የሚያፈል
ቅ፣ መናን ከሰማይ የሚያወርድ፣ማንም
ሊፈታው ያልቻለውን ለዘመናት ያስለቀ
ሰንን በመሰፍኑ የታተመውን ማህተም
የፈታ ኃያል ጌታ ነው። ለእርሱ የሚሳነ
ው ምንም ነገር የለም። በሁሉም ላይ
ኤልሻዳይ ነው። ለዚህም ነው ሐዋርያ
ው «ከኃይለኛውና ከክንዱ በታች ራሳች
ሁን አዋርዱ» ያለው እርሱ ስለእኛ ይ
ዋጋልና አንችለውም ያልነው እኛነታችን
ን ያዛለውን የጠላት ፍላጻ በአምላካችን
ኃይል ሲደመሰስ እናያለን አይተንማል።

ነገር ግን «ሥጋ ለባሹን ክንዱ የሚያደ
ርግ የተረገመ ይሁን» እንደተባለ ላያዋ
ጣን በሥጋ ለባሽ ላይ ብንታመን ውጤ
ቱ ያው ሞት ነውና እናስብበት። ማንም
የሚመካ ቢኖር በእግዚአብሔር ይመካ
ያን ጊዜ ባህሩም ይከፈላል፣ ጠላትም
ይሰጥማል፣ ወጥመዱም ይሰበራል፣ ያስ
ጨነቀን ታላቅ ተራራ በጌታ ፊት ደልዳ
ላ ሜዳ ይሆናል ...ሌላም ሌላም ታላላ
ቅ ታምራት ብቻውን ያደርጋል። ሁሉ
በጌታ ዐይን ቀላል ነውና።

**ጽዮናዊት**
**ከሐመረ ኖህ ሰ\ት\ቤት**

---

## <u>God's will</u>

What drives your life? Have you asked yourself that question?
Everyone's life is driven by something. Some are driven by money others by passion, or by the need to please people or just themselves. So ask yourself again, what is the true driving force in your life?
Are you led by some unconscious belief or do circumstances guide your life? Whatever it is, it's certain that these forces lead you to the same dead end – unfulfilled life & unnecessary stress. You find yourself hopping from one point to another, in pursuit of your purpose, never to attain satisfaction. Have you asked why?
The answer is simple – it is because you are living carelessly, not understanding your true purpose in life & not making God the center of your life.
Unsympathetic you may say, but you will appreciate the depth of that answer when you read further.

So this takes us to the second set of questions –
<u>What is your purpose in life and what is God's will for you?</u>

Do you ask yourself **WHY** before you get involved in something? Do you ask how the task you are about to start will help you fulfill God's purpose? Or do you just get into things carelessly?
Ephesians 5:17 says: "***Do not be foolish, but understand what the Lord's will is***".
In other words, the apostle Paul is telling us not to live carelessly, making sure we understand what God's purpose is for our life.

Many of us desire to do God's will, but we struggle because we don't know what His will is. What does God want us to do? How would His purpose be revealed to us? Wouldn't be easier if we had some clear guidance from God, to tell us what to do, where to work, where to live, who to marry etc.?
Knowing God's will is difficult, but

even if we can't find Him in the burning bush like Moses, He has left us His words to live by. Thanks to the Almighty, the Bible is now our burning bush! "***Your word is a lamp to my feet and a light to my path***" says the Psalmist in Psalm 119:105.

There are two key principles for knowing God's will:

1. To make sure what we are praying for or what we are about to do is something that is supported by the bible
2. To make sure what we are about to do glorifies God and helps us grow spiritually

These two things have to be aligned together. If these things are true and God is still not giving us what we are asking, then it is likely not God's will or it is taking a while longer for a reason.

God rarely gives people a direct and specific of information. He allows us to make choices regarding our circumstances. The only decision God does not want us to make is the decision to sin or resist His will. If we are walking closely with the Lord and truly desire His will for our life – God will place His desires in our heart. When deciding between two alternatives that we have been praying about, sometimes one of the options will give us a greater peace. That option is probably His will. The key here is wanting God's will, not our own. If the bible does not speak against it and it can genuinely benefit us spiritually - then the bible gives us the permission to make decisions and follow our hearts. But we have to remember, God's will, first and foremost, is that we have a relationship with Him. This means learning to read His word everyday, praying, seeking Him & keeping Him first in our life.

Let us trust God in faith that He will accomplish His will in our lives.
One of my favorite bible verses is Proverbs 3:5-6 "***Trust in the Lord with all your heart and lean not on your own understanding; in all your ways acknowledge Him and He will make your paths straight***". Amen! How comforting is that?
"In all your heart" means without a doubt, in all trust Him 100%
"Lean not on your own understanding" means let's not follow our own thoughts or feelings. We think we know better, but He knows what is best for us.
"Acknowledge Him" – this means know Him, understand His word, and follow Him. Nodding in God's direction is just not enough. We must know Him by living closely with Him, relating to Him personally in every aspect of our life and "He will make our path straight" – He will direct our life, meaning we see the smaller pieces fitting in the big puzzle & we see ourselves going in the right track.

Brothers and Sisters, we are in good hands. What lies ahead for us when we choose God's way, are some fantastic things listed in the book of Proverbs We get these when we solely stay in God's path (Read Proverbs 3:1-15)

- Long life & peace (verse 2)
- Favor in the sight of God & man (verse 4)
- Direction from God (verse 6)
- Health and strength (verse 8)
- Abundance (verse 10)
- Happiness (verse 13)
- Wisdom (verse 15)

The person who trusts, honors and fears the Lord will find these things.

Our greatest calling of all is to be in love and stay in love with God.
When we do, we will be able to repeat what David said in Psalms 27: 4 – “***One thing I ask of the Lord, this is what I seek: that I may dwell in the house of the Lord all the days of my life, to gaze upon the beauty of the Lord and to seek Him in His temple***”

So we conclude - God’s ultimate purpose for us is that He would be glorified and that the gospel and God’s kingdom would be advanced. In everything we do, let us remember that His name is being elevated & that it is pleasing to Him. Let us put God first in our life. Amen.

*Written by Tsedale Mariam*

---

## የታረደው በግ

**የታረደውን በግ ኑ እናመስግነው**
**ድንቅ ውለታ ነው ለሰው ልጅ የዋለው**
**የምስጋና መስዋእት አቅርቡለት ለሱ**
**ባለውለታ ነው ስሙን አወድሱ**
**አምላክ ሆኖ ሳለ ሰው ሆኖ ለመጣው**
**አቅርቡለት መባ ለሱ እንደሚገባው**
**እልል እልል በሉ ዘመሩ በአንድነት**
**ሌላ የምንሰጠው ምንም የለም በእውነት**
**ሕዝብና አሕዛብ ባንድነት ነጭ ለብሰው**
**የዘንባባ ቅጠል በእጃቸውም ይዘው**
**በበጉ ዙፋን ፊት ቆሙ ለምስጋና**
**አድሎ የሌለው ድንቅ አምላክ ነውና።**
**እጅግ የበረታ ጥበቡ ጥልቅ ነው**
**ዙፋኑም ከፍ ያለ ከአእምሮ በላይ ነው**
**በዚ ድንቅ ሥራው የተማረካችሁ**
**ምስጋናን አሰሙ በአንድነት ሆናችሁ**
**በቀራንዮ ላይ ሕይወቱን የሰጠው**
**ከቶ እንደሱ ማነው ሰውን የወደደው**
**አወድሱ ስሙን ውለታ ያለባችሁ**
**ከሱ እጅ በረከት የተቀበላችሁ።**
**ለታረደው በግ አምጡ ምስጋናውን**
**በክብሩ ዙፋን ፊት የሚቀርብ መባውን**
**አዲስ አዲስ ቅኔ እለት እለት ይዘን**
**የቀራንዮን በግ እናመልከዋለን።**
**ሱራፌል ኪሩቤል የሰማይ መላእክት**
**ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው**
**የሚያመስግኑት**
**እኛ እንድናመልከው እሱ ፈቅዶአልና**
**ሃሌ ሉያ ለርሱ ይድረሰው ምስጋና**
**ሃሌ ሉያ በሉ ይገባዋልና**
**ሃሌ ሃሌ ሉያ ይድረሰው ምስጋና።**

**ከአፀደ ማርያም**

---

## እነሆ ጌታዬ ከደጄ ቆሟል

**ትሕትናን ተላብሶ እኔን ሲጠይቀኝ**
**እያለ ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ**
**አልጣህ ከቤቴ ከእኔ ጋር ሁንልኝ**
**ጌታዬ እያንኳኳ እንደ ደጅ ጠኝ**
**እኔ ግን አየኋት የራሴን ሰውነት**
**ቆሸሻለች በእውነት ምንም ንፁህ የላት**
**የጌቶችን ጌታ ከፍቶ ለማስገባት**
**እንዴት ትነጻለች እንዴትስ ልጠባት**
**ወንጌሉን ለማድመጥ ልቤ ይከፈት**
**የሰጠኝን ሁሉ ትዕዛዙን ላክብራት**
**እስከ መቼ ድረስ ሸሸቼ በፍርሃት**
**በንስሐም ልታጠብ በጸሎትም ልትጋ**

ላዝለው በስግደት ይህን ከንቱ ሥጋ
ትቀበለው ነፍሴም የዕለት ምግቧን
ትብላልኝ ሥጋውን ትጠጣልኝ ደሙን
በመስቀል ላይ ሆኖ ለእርሷ የሰዋውን
ግባልኝ ልበለው እኔም በእልልታ
ከደጄ ለቆመው ለዓለም መከታ
እራቱንም ይብላ ከእኔ ጋራ ጌታ
ይክበር ይንገሥበት በቤቴ በረከት

ኑሮዬም ይሁንልኝ ሰላም የሞላበት
ከእኔ ጋራ ይኑር የዓለም መድኃኒት
እኔም ልገዛለት እስከ ሞቴ ዕለት
ዕለት ከዕለት እየመገበ የወንጌሉን ቃል
ኃጢአቴን ሊያነጻኝ በደሙ ኃይል
እነሆ ጌታዬ ከደጄ ቆሟል

ሃይማኖት ገ/ሥላሴ